# የየጁ ደብተራ ቅኔው ሲጎልበት ቀረርቶ ሞላበት

***ስሜነህ ባዘዘው***

መቼም የሃገራችን መጻዊ ህልውናና ለዘመናት ያላባራው የህዝባችን መከራ እያስጨነቀን፤ መላ ፍለጋ እንደየአቅማችን የምንባዝን ወገኖች ቁጥራችን ቀላል አይደለም።

የመላ ፍለጋው አንዱ መንገድ ደግሞ ምክክርና ሃሳብ መለዋወጥ ነው። ከትናት ተምሮ፤ በዛሬ ሞክሮ፤ ለነገ መክሮ ማደር የውጤታማነት ዋናው ጉዳና ነው ይባላልና በሰጥቶ መቀበል መርህ የተቃኘ የሃሳብ ልውውጥ ሊዳብር የሚገባው ልምድ ነው። ይሁንና እየለመደብን የመጣው የሃሳብ ልውውጥ ዘይቤ ግን ከሰጥቶ መቀበል ይልቅ በጥሎ ማለፍ መርህ ላይ የተመሰረተ መሆኑ የመከራችንን ዘመን እያረዘመው ነው።

በኔ ዕምነት አንድ ሰው በአንድ ጉዳይ ላይ ለመጻፍ ሲነሳ፤ አንድና ዋና መርህን ተመርኩዞ መሆን ይገባው ይመስለኛል። እሱም አንባቢውን ማክበር ነው!። በሌላ አገላለጽ ለንባብ የምናበቃው ጽሁፍ ውስጥ ያለው ፍሬ ሃሳብ የአንባቢን ውድ ግዜ የሚመጥንና የአንባቢን የማስተዋል አቅም ዝቅ አድርጎ የማይመለከት መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ። አለበለዚያ በራሳችን ብዕር የራሳችንን መቃብር የመቆፈር ያህል ጥፋት እንሰራለን።

ውድ አንባቢያን፡ በመርህ አጨናነቅኳችሁ መሰለኝ። ይቅርታ! አድርጉልኝ።ወድጄ አይደለም፡፡ የአንድ ግለሰብ የሰሞኑ ጉንጭ አልፋ (ቀለም አጥፊ) ጽሁፎች አሳዝነውኝ ነው።

በሻቢያ እርዳታ የሚደረግ ትግል በአፍንጫዬ ይውጣ የሚሉ ወገኖች ሃሳባቸውን በተለያየ መልክ ሲገልጹ ቆይተዋል፤ አብዛኞች የአመለካከት ልዩነታቸውን በሰለጠነ መልክ "በልዩነት" ይዘው የራሳቸውን ስራ እየሰሩ ነው። ይህ ደግሞ የብስለት ምልክት ነው።

ጥቂቶቹ ደግሞ አሁንም ድረስ በየሶስት ቀኑ ውሃ የማይቋጥር ሃተታ እያቀረቡ አንባቢን እያሰለቹ ናቸው። ከላይ ልገልጽ የፈለኩትም ይህንኑ ነው። በአጥር እየተንጠራሩ እንደሚሞላለጩ ቂመኛና ነገረኛ ጎርቤቶች አይነት በየሶስት ቀኑ ፍሬ ፈርሲኪ ነገር እየለቀለቁ የአንባቢን ግዜ መሻማት እራስን ትዝብት ውስጥ ይከታል።

ደምስ ከሚባል ሰው የሰሞኑ እንቅስቃሴ የተገነዘብኩት ይህንኑ ነው፡፤ አቶ ደምስ በኤርትራ በኩል የሚደረገውን ትግል በመቃወም በተከታታይ በርካታ ጽሁፎችን አስነብቦናል። በአንድ ወቅት፤ በኤርትራ ምድር ተገኝቼ አየሁት ያለውን፤ ታዘብኩት ያለውን፤ ጠላሁት ያለውን፤ አሳዘነኝ ያለውን ....ሁሉንም አቅሙ በፈቀደ መጠን በተደጋጋሚ ሲያስነብበን እኛም የጻፈውን ሁሉ በጥሞና አንብበናል። የሱ ኃላፊነትም እዚህ ድረስ ይመስለኛል፡፤ የጻፍኩትን አንብቡልኝ እንጂ የታዘብኩት ታዘቡልኝ፤ የጠላሁትን ጥሉልኝ፤ ሊለን አይችልም።አይገባም፡

ደግሞም እኮ! እሱ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብቱን ተጥቅሞ ጽሁፉን እንዳስነበበን ሁሉ ሌሎችም ይህንኑ መብታቸውን ተጠቅመው ስለ እሱ ማንነትና ምንነት ስለ ምክንያት-አልባ የኤርትራ ጉዞው! ተያይዞም ስለ ግለሰባዊ ባህሪው፤ .... አስነብበውናልና ግራ ቀኙን አመዛዝነን የራሳችንን ግንዛቤ እንድንይዝ ፋታ ቢሰጠን ጥሩ ነበር። ሊሆን ግን አልቻለም።

የአቶ ደምስ የኤርትራ ቆይታ ተመክሮ ጠቅላላ ድምር "ሻቢያ የሚሰራው ኢትዮጵያን ለማጥፋት ነው " በሚል ዕምነት ላይ ያጠነጠነ እንደሆነ በየጽሁፉ ላይ በተደጋጋሚ ገልጾታል። የሰሞኑ ሩጫው ደግሞ የአርበኞች ግንቦት ሰባት ሰዎችን ዱካ እየተከተለ እንቅስቃሴያቸውን ሁሉ ማጠልሸት ነው። ምክንያታዊ ተቃውሞ ከድጋፍ ይቆጠራል ይባላል፡፤አራሚ ነውና። ምክንያታዊ ያልሆነ ተቃውሞ ግን ተራ ማጠልሸት ነው። ተራ ማጠልሸት ደግሞ የተራነት መገለጫ ነው።

አቶ ደምስ በተከታታይ የጻፋቸው ጽሁፎቹ በሙሉ እየሮጠ የጻፋቸው እስኪመስሉ ድረስ መረጋጋት አይታይባቸውም። የጭብጥ መፋለስና በመሰለኝና በደሳለኝ የተሰነዘሩ፤ የተዋከቡ ሃሳቦች በዝተውባቸዋል። አንባቢን ይቆረቁረው ይሆን? ሳይል ከቁንጽል ነገር ተነስቶ ግዙፍ ድምዳሜ ላይ ዘፍ ይላል።

በተለይ በቅርቡ "በሬ የሚያስወልደው የተከፈለው ነው !" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጽሁፍ ከርዕሱ ጀምሮ የወረደና አንባቢን የናቀ ስለሆነብኝ በመጠኑም ቢሆን ቢያረጋጋው ብዬ ይህችን አስተያየት ልጽፍ ተነሳሁ።

**ልቀጥል፡-**

የደምስን ተከታታይ ጽሁፎች ሳነብ በተለይ የአጻጻፍ ስልቱ ዝብርቅርቅ ያለና ግራ የሚያጋባ ሆኖብኛል። በነባራዊ ዕውነታ (ፋክት)ና በምናቡ ዓለም ልቦለድ መካከል ያለውን ግዙፍ ልዩነት የተረዳው አይመስልም፡፤

የዴምህቱ መሪ ሞላ አስገዶም ከትናንት በስቲያ እስከ ዛሬ በሚል ርዕስ ያስነበበን ጽሁፍ ታሪክ ቀመስ ልቦለድ ነው። በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ የፈጠራ ሥራ (የምናብ ውልድ) እንደሚባለው ነው። ደምስም የሞላን ኩብለላ እንደ ጭብጥ ወስዶ የራሱን የፈጠራ ሴራ አክሎበት አቀረበው። ሞላ ሲኮበልል ደምስ በምናቡ አዲስ አበቤ ጓዳ ገብቶ

- ኢትዮጵያ ውስጥ አዲሱን የ2008 ዓ.ም አመት ለመቀበል ሁሉም በየቤቱ እንደአቅሙ ሽር ጉድ እያለ ነው ። በመላ ሃገሪቷ ሜዳና ሸንተረር ፤ ሸለቆና ሜዳ ፤ አደይ አበባው ፈንድቷል ።

ይለናል።በዚህ ብቻ አይበቃውም።

- የመጨረሻው ሰአት ደርሶ ሻእቢያ ትእዛዝ ሰጠ ። ትእዛዝ የተሰጠው ጦር ውስጥ ከየአቅጣጫው ግርግር ተፈጠረ ። ከዚህም ከዚያም ጥይት ተተኮሰ ። እነሞላ አስገዶምን በጥይት ርቀት እንዲጠብቁ ፤ ትእዛዝ የተሰጣቸው የሻእቢያ አልሞ ተኳሾች (Snipers) ፤ ከተዋጊዎቹ በሚተኮሱት ጥይቶች ሬሳቸው እዚህም እዚያም ጠብ ጠብ ማለት ጀመረ ።

በማለት ሞላና አስከትሎት የሄደው ወታደር የሰራውን ጀብዱ ይተርክልናል። ለመሆኑ ይህን ጽሁፍ እንደምን እንቀበለው? እንደ ልቦለድ ? ወይስ እንደ ጋዜጠኛ ሪፖርት? በኔ ዕምነት ይሄ አንባቢን መናቅ ነው፡፡

አቶ ደምስ ሆይ! ለመሆኑ አብረን የሰማነውን የሞላን ኩብለላ በሚገርም ልቦለድ ከሸነህ ስታቀርብ እያየንህ፤ ኤርትራ በነበርኩበት ግዜ ታዘብኩት አየሁት እያልክ የምትነግረንን ሁሉ እንዴ ልናምን እንችላለን? ሩቅ አልሞ ቅርብ መሳት ይሉሃል ይህ ነው። ደራሲና ጋዜጠኛ ደምስ!።

**<u>ደምስ እንደ ታሪክ አሰረጂና መስካሪ!</u>**

ልብ ብላችሁ እንደሁ የአቶ ደምስ የመጀመሪያ ሰሞን ጽሁፎቹ አቀራረብ የ"ታሪክ አሰረጂ" ወይም የ"መስካሪ" አይነት ነበር። ኤርትራ በነበርኩ ጊዜ እንዲህ ሆነ! በዚህ ወጣ! በዚህ ወረደ...በሚል ለጉዳዩ ከማንም በላይ ቅርበት አለኝ ለማለት መፈለጉን በሚያሳብቅ መልክ ጮክ ያለ ትርክት አስነብቦናል።(ልቦለድ ስለመሆናቸው ያደረብን ጥርጣሬ እንዳለ ሆኖ) ።

ታሪክ እራሱን ሲደግም እንጂ በሰው አንደበት ሲደጋገም አያምርምና አቶ ደምስም እንዳይሰለች በመስጋት ይመስላል ስልታዊ ማፈግፈግ በማድረግ ከታሪክ አሰረጅነት ወደ ሪፖርተርነት ተሸጋገረ።

**<u>ደምስ እንደ ሪፖርተር</u>**

ደምስ የታሪክ አስረጂነት ምዕራፍ በተከታታይ ጽሁፎቹ አቅርቦ ሲጨርስ ደግሞ ሌላ ምዕራፍ ከፈተ፡-ሪፖርተርነት! በኤርትራ ውስጥ የሚካሄደውን እንቅስቃሴ፤ የአርበኞች ግንቦት ሰባትና የሌሎቹንም ድርጅቶች አቋም፤ የስብሰባ ሂደትና ውሳኔ በፈርጅ በፈርጁ በቀጥታ ያስተላልፍልን ጀመር። በመሰለኝና በደሳለኝ ።ታሪክ አሰረጂውና ሪፖርተሩ ደምስ በዚህ አላበቃም፡ ሌላ ምዕራፍ ገለጠ፡ ነብይነት

**<u>ደምስ እንደ ነብይ</u>**

ከአቶ ደምስ ትንበያዎች ጥቂቶቹ፡-

ትንቢተ ደምስ ከቁጥር 0 እስከ 0

- ከላይ በገለፅኩት ዴምህት የሻእቢያ የትሮይ ፈረስ ዕሁፌም ላይ የዚህን "አገር አድን የጋራ ንቅናቄ" መቋቋም አስመልክቶ ፤ የሚከተለውን ትንበያ አድርጌ ነበር ። "የአዲሱ ትብብር ሊቀ-መንበርነት ስልጣን ለቀድሞው ግንቦት 7 መሪ ይሰጣል ።

ትንቢተ ደምስ ከቁጥር oo እስከ oo

- እንደተለመደው አንድ ጉዳይ ልተንብይና የዛሬውን ፅሁፌን ላብቃ ። አሚረተ አትበሉኝ እንጂ ፤ በሻእቢያ ምክንያት ፤ በቅርቡ ከዚህ ከአሜሪካ በሄዱት ወገኖች ላይ ፤ ሊከሰት የሚችል አዲስ ሁኔታ ይኖራል ። በዚህ ላይ ከሻእቢያ ጋር የሚደረጉ ስምምነቶች ሁሉ ፤ ወርድና ስፋታቸው በሻእቢያ እየተለኩ ስለሚዘጋጁ ፤ የፈለጉትና ያሰቡት ስለማይሆን ፤ ከሚቀጥለው የኢትዮጵያ አዲስ አመት በፊት ፤ አስመራን ለቀው ወደየመጡበት ይመለሳሉ፡-

የአቶ ደምስ አንደኛው ትንቢቱ የጥምረቱ ሊቀመንበርነት ለቀድሞው የግንቦት ሰባት ሊቀመንበር ይሰጣል ያለው ነው።ይህቺ ነች ጨዋታ አትሉም?፤ አቶ ደምስ ሆይ! የግምትና የትንቢትን ልዩነት አታውቅምን? ግምት ከነባራዊ ጭብጥ ተነስቶ በቀጣይ የሚሆነው መናገር ነው። ትንቢት ግን እንዳንተ የታደሉት ብቻ በጸጋ የሚያገኙት ነው። እናም ነብዩ ደምስ ሆይ ዶክተር ብርሃኑ የጥምረቱ ሊቀመንበር እንደሚሆኑ ሁላችንም ገምተናልና ነብይነትክን እንዳንሻማ ሲጋን።

አቶ ደምስ ከሰማዩ ጌታ ይሁን ከምድሩ…ከየት እንደተሰጠው ባይገልጽልንም የትንበያ ጸጋውን ተጥቅሞ እንሆ ያለንን ሌላኛውን ትንቢት ስንመረምር "ከአዲስ አመት በፊት ወደ አሜሪካ ይመለሳሉ" የሚለው ትንቢት ምንጭ ዘሃበሻ ድህረ ገጽ መሆኑን እንረዳለን። http://www.zehabesha.com/amharic/archives/46786 አቶ ደምስ ተነበይኩ ያለበት ቀንና የዘሃበሻ ዜና የወጣበት ቀን አንድ ቀን መሆኑን ልብ ይሏል።

ዘሃበሻ ድህረ ገጽ "አስመራ የገቡት አቶ ነአምን ዘለቀ በሚኒሶታው የአርበኞች ግንቦት 7 ገቢ ማሰባሰቢያ ላይ እንደሚገኙ ተገለጸ" በሚል አቶ ነአምን ከአስመራ ሳይነሱ ለንባብ ያቀረበውን ዜና አቶ ደምስ ወደ ትንቢትንነት ቀይሮ ይዞልን ቀርቧል። ታዲያ ይሄን ምን እንበለው፡ ዜና-ቀመስ ትንቢት? ለኔ ይሄ በጣም የወረደ ተራ ማጭበርበር ነው።

የሚገርመው ደግሞ ራሱ ተነበይኩ ማለቱን ዘንግቶ ይህንኑ ጉዳይ እንደ ጋዜጠኛ ሪፖርት ሲያደርግ

- ባለፈው ወር ጓዛቸውን ጠቅልለው ገቡ ፤ ከተባሉት ሶስት የአሜሪካ ዘማች በረኸኞች ውስጥ ፤ አንዱ ትላንት ወደ አርብ ወደ አሜሪካ መግባት ነበረባቸው ። ከሞላ አስገዶም ጥሎ መሄድ ጋር በተያያዘ የሚጣራ ጉዳይ ስላለ ፤ ላልተወሰን ጊዜ ከአስመራ እንዳይወጡ ተደርጓል

ብሎናል። መጀመሪያ ከአዲስ አመት በፊት ይመለሳሉ ሲል የዘሃበሻን ዜና ተነበየ፤ ቀጠለና ከሞላ ጋር በተያያዘ ላልተወሰነ ግዜ እንዲቆዩ ተደረገ ሲል ሪፖርት አደረገ። ባጠቃላይ አቶ ደምስ አንዴ ታሪክ አስረጂ፤ ሌላ ግዜ ሪፖርተር ጋዜጠኛ፤ ሲለው ደግሞ ነብይ እየሆነ ፍጽም የተምታታበት አካሄዱ ከማንም በላይ እራሱ ግራ እንደገባው የሚያመላክት ይመስለኛል።

በቅርቡ በጻፈው ጽሁፍ ላይ ደግሞ ጥቂት ልበልና ሃሳቤን ላጠቃል።

"በሬ የሚያስወልደው የተከፈለው ነው !" በሚል ርዕስ በቅርቡ ያስነበበን ጽሁፍ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ቁንጽል ከሆነ ነገር ላይ ተነስቶ ግዙፍ ድምዳሜ ላይ የሚወድቅበት፤ የአንባቢን የማገናዘብ አቅም ከመጤፍ ያልቆጠረበት፤ ያልተባለ ነገር ተብሏል ብሎ እንደመረጃ የሚጠቅስበት ጽሁፍ ነው።

በዚህ ጽሁፉ ያንሸራሸራቸው ሃሳቦችን ነቅሰን እንመልከት፡

- አሁን ደሞ ያ ሁሉ ጭብጨባ ተደርጎ፤ ጉሮ ወሸባዬ ተዘፍኖ ሄደው፤ ዛሬ የተመለሱት ዘማች አቶ ነአምን ዘለቀ፤ እንደነገሩን የዘመቻ ተልእኳቸውን አጠናቀዋል። በዘመቱ በሁለተኛ ወራቸው በረኃ የገቡት ዘማች "ተልእኮዬን ጨርሻለሁ" ብለው ሲመለሱ ትንሽ ግር ማለቱ አልቀረም።

የአቶ ነአምን በድርጅቱ ያላቸው ኃላፊነት የዓለም አቀፍ አመራር የዉጭ ግንኙነት ሃላፊ ነው። ይህ ማለት ምድብ የስራ ቦታችቸው ውጭ እንደሚሆን ግልጽ ሆኖ ሳለ አቶ ደምስ ተራ ጸጉር ስንጠቃ ውስጥ ገብቶ "ተልእኮዬን ጨርሻለሁ" አሉ ብሎ መሳለቁ የሚያሳዝን ነው።

- ሻእቢያ ወይም ኤርትራ፤ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የStakeholderነት (ባለድርሻ አካልነት) መብት አለው ሲሉ ተናግረዋል።

ይህንን አሁንም ለአንባቢ ፍርዱን እሰጣለሁ

http://amharic.voanews.com/content/gimbot-seven-discussion-ethiopia-/2979458.html

አቶ ነአምን ለ40 ደቂቃ ያህል ከቪኦኤ ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ በኢትዮጵያ ጉዳይ ሻቢያ ባለድርሻ ነው። ያሉበትን ክፍል ላገኝ አልቻልኩም። አቶ ደምስ ከየት አምጥቶ ይህንን ሊል እንደቻለ ሊገባኝ አልቻለም። ምናልባት “ወደፊት ህዝብ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የሚመርጠው የኢትዮጵያ መንግስት ከኤርትራ መንግስት ጋር በጋራ ጥቅም ላይ ተመካክሮ የሚሰራበት ይሆናል” በማለት የተናገሩትን አዛብቶ ለማቅረብ ታስቦ ከሆነ ይህም አንባቢን መናቅ ነው።

- ግንቦቶች እንደግንቦት 7 ድርጅት ፤ ከሻእቢያ ጋር የመሰረታችሁት ፍቅር የራሳችሁ ሊሆን ይችላል ። በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ፤ ከማንም ጋር ለመስማማት ግን ፤ ምንም አይነት ስልጣንም Mandate እንደሌላችሁ በግልፅ ልታውቁት ይገባል ።

የአርበኞች ግንቦት ሰባት አመራሮች የህዝብ ውክልና ስለሌለን በሃገራዊ ጉዳይ ላይ ከሻቢያም ሆነ ከማንም አካል ጋር ልንደራደር አንችልም። አናደርገውም።በማለት በተደጋጋሚ ሲገልጹት የነበረውን ጉዳይ ዛሬ አቶ ደምስ የራሱ ማሳሰቢያ አድርጎ ማቅረቡ የሚለው አልቆበት ጽሁፉን ለማስረዘም ያህል የሰነዘረው ካልሆነ ሌላ ምንም ትርጉም የለውም። የየጁ ደብተራ ቅኔው ሲጎልበት ቀረርቶ ሞላበት ይሏል ይህ ነው። የቬጋስ ደብተራ አይባል ነገር።

- ግንቦት ሰባት ሻእቢያን ባለድርሻ አካል ካደረገ ፤ ዋና ፅ/ቤታቸውን አስመራ ያደረጉት የኦሮሞ ነፃ አውጪና የኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባሮች ፤ የመገንጠል ጥያቄ ባቀረቡባቸው የኢትዮጵያ ግዛቶች ላይ ፤ ለሻእቢያ ምን ያህል ባለ ድርሻነት ሰጥተውት ይሆን ?

ይህም ከላይ ከገለጽኩት ጉንጭ አልፋ ጥያቄ ጋር ተያያዥ ነው።

- ትብብሩ ተቋቋመ በተባለ ማግስት ከሞላ መሄድ ጋር፤ ፍርክስክሱ ወጣ

ከቁንጽል ሃሳብ ተነስቶ ግዙፍ ድምዳሜ መድረስ ይሏል ይህ ነው። ይህስ ትንቢት ይሆን ወይስ ትቢት? የሚገርመው አቶ ደምስ እዚህ ጭፍን ድምዳሜ ላይ ያደረሰውን ሳይንሳዊ ትንተና ሲያስቀምጥ፡- የኢትዮጵያ ሰራዊት የተፈታው ከኮለኔል መንግስቱ ኃይለማሪያም ኩብለላ በኋላ ነው ይለናል። ሥጋ ቁጠር ቢሉት ሰውየውን “ጣፉያ አንድ” ብሎ ጀመረ አሉ፡፡ምነዋ አቶ ደምስ እንዲህ አይነት ደካማ ትንተና ከገበሬው ልጅ ከሞላም አንጠብቅ።

- አንዳንድ ሰዎች ዩናይትድ ኔሽን 20 ሺህ ይገመታሉ ብሏል ይሉናል ። ዩናይትድ ኔሽን አስመራ ሄዶ ተዋጊዎቹን አስልፎ ቆጥሯል ?

አቶ ደምስ ግንቦት ሰባት በዴምህት ላይ ሊፈናጠጥ አስቦ ነበር ብሎ ግንቦት ሰባትን አኮስሶ ዴምህትን ማግዘፉን ዘንግቶ አሁን ደግሞ ዴምህትም ዋጋ የለውም ይለናል። የተባበሩት መንግስታትም አሃዝ ውሸት ነው ይለናል።

ሌላውን ለአንባቢ ፍርድ ልተወውና ጽሁፌን ልቋጭ፤ ከዚያ በፊት ግን አቶ ደምስ ሆይ! ይጠቅምሃል ያልኩት ጥቂት ምክሮች ላካፍልህ። አንባቢህን አክብር። በመሰለኝና በደሳለኝ፡ አትጻፍ። ልቦለድና እውነታን አትቀላቅል።ውስጥህ መጻፍ አለብህ እስኪልህ ጠብቅ እንጂ መጻፍ አለብኝ ብለህ አትጻፍ።

“እንግዳው ብዙ ጠላው ቀጭን ነው” እንዲሉ አንተም በሳምንት ሶስትና አራት ጽሁፍ ለማምረት ስትል እውነታውን በልቦለድ፤ ሪፖርቱን በትንቢት እያቀጣጠንክ በምትለቀው ጽሁፍ ትዝብት ውስጥ አትውደቅ። የየጁ ደብተራ ቅኔው ሲጎልበት ቀረቶ ሞላበት እንደተባለው የሰሞኑ ጽሁፍህ ቀረርቶ በዝቶበታል።

ቸር ይግጠመን

**semenehbazezew@gmail.com**